# Kinijit International Council

## ቅንጅት ዓለምአቀፍ ላዕላይ ምክርቤት

P. O. Box 10441 Marina Del Rey CA 90295 USA www.kinijitcouncil.org


## በሀገራችን የተጀመረውን የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ አጠናክሮ ለማራመድ ጊዜው አሁን ነው

እንጅነር ሀይሉ ሻውል፤ የቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ፕሬዘደንት ታህሳስ 1 2000 ዓ ም በአምስት የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ላይ ታሪካዊ የሆነ የሥራ እቀባ በተመለከተ መመሪያ ስጥተዋል። በዚሁ መግለጫ እገዳዉን ያስፈለገበትን መክንያቶች በትክክል አሳማኝና ዘርዘር ባለ ሁኔታ አቅርበዉታል። ማእቀቡም የቅንጅት ላእላይ ምክር ቤት የአምስቱን አባላት ተግባር፤ ፀባያና የወደፊት ዓላማ መርምሮና አጥንቶ ውሳኔ እስከሚስጥ እንደሆነ ተገልፆአል፡፤ በጣም የሚያሳዝነዉ በዚህ ፈታኝ ወቅት የችግሩ መንሣኤ የግለሰቦች የሥልጣን ጥማት ሆኖ መገኘቱ ነው።

ሆኖም የፕሬዘንድቱ እርምጃ ቆራጥ፤ ትክክለኛና ወቅታዊ በመሆኑ የተፈጠረዉን ችግር ሊገታው ይችላል ብለን እናምናለን። በሀገራችን መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር ያነቃነቀውን፤ በውጭው ዓለምም እንደዚሁ ደጋፊዎቹን በአንድነት ያስተባበረውን መሠረታዊ የቅንጅት መርሆዎች ለድርድር ማቅረብና ሌሎች የአመራርን ህብረት የሚያናጉ፤ ተጠያቂነትን፤ የወደፊት እቅዱንና ፍላጎቱን ሊያደፈርሱ የሚችሉ ሁኔታዎች በአግባቡና በፍጥነት መገታት አለባቸው። የአንድ መሪ ዋነኛው ተግባርም ትክክለኛውን እርምጃ በተፈለገው ጊዜና ቦታ ለትክክለኛ ምክንያቶች መውሰድ ነው። በመጨረሻም ለዚህ ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ትክክለኛ ዳኞቹ ይሆናሉ።

በመመሪያው ላይ እንደተገለጸው ቅንጅት ጠንካራ ፓርቲ ሆኖ ሊወጣ የቻለው በመሪዎቹ ቆራጥነትና ለዓመታት ባካሄዱዋቸው ሰላማዊ ትግል ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብም የቅንጅትን አጠቃላይ መርሆዎችን ለግለሰብ ነፃነት መከበር፤ ለሰላማዊ ትግል፤ ለብሔራዊ እርቅ፤ ለሕግ የበላይነት፤ ለብዙሃን ፓርቲ ዲሞክራሲ፤ የፖለቲካ ልዩነቶችን በውይይት መፍታትና ስምምነቶችን ማድረግ በሙሉ ልቡ አቅፎ በመደገፉም ጭምር ነው።

ቅንጅት የፈጠረው የአሠራር ሥልት ለፓርቲው አፋጣኝ እድገት ዋነኛው አንቀሳቃሽ ሀይሉ ሲሆን ለመጭውም ትውልድ ድርጅቱ የቀመለትን ዓላማ ለማራመጃ መሠረት ሆኖ እንድሚኖር አያጠራጥርም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘር፤ ሃይማኖት፤ ጾታ፤ እድሜና የፖለቲካ ልዩነቶች ሳያለያየው ቅንጅትን የራሱ አድርጎ ስለሚቆጥረው ይንከባከበዋል፤ ይደግፈዋል፤ ይጠብቀዋልም። ማንም ግለሰብ፤ ድርጅት ወይንም ማናቸውም ሀይል ሊያፈርሰው አይችልም። የእኛ ፋንታ የወደፊት ሂደቱን መቀየር ሳይሆን አስፈላጊውን ድጋፍ በተጠየቅን ጊዜ መስጠት ነው።

# Kinijit International Council

# ቅንጅት ዓለምአቀፍ ላዕላይ ምክርቤት

P. O. Box 10441 Marina Del Rey CA 90295 USA    www.kinijitcouncil.org


በአሁኑ ወቅት በሰሜን አሜሪካ እንደዚሁም በኢትዮጵያ የሚታየው አለመግባባት፤ የስም ማጥፋት ዘመቻና ወገንተኝነት ማናችንንም አይጠቅምም። የሚጠቀመው የገዥው ወገንንና የራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ ለማራመድ የሚፈልጉ ግለሰቦችና ቡድኖችን ነው። በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ግን የተከሰተው ችግር የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሰላም፤ ለሕግ የበላይነት፤ ለነፃነት፤ በቡዝሃን ፓርቲዎች ላይ የተመሠረተ ዲሞክራክራቲክ ሕብረተሰብ ለመመሥረት የሚያደርገው ትግል ላይ አሉታዊ ተጽኖ እንዳለው ነው። መርሆዎችን በሥራ ለመተርጎም የድርጅቱ መሪዎችና የአባላት  ብቃት፤ ዝግጁነትና ፈቃደኝነት አስፈላጊ ነው። እነዚህን መስፈርቶች በተቀነባብረ መንገድ ተጠቅሞ  ትግሉ የሚጠይቀውን መሥዋእትነት በመክፈል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መቆም ያስፈልጋል።

ስለሆነም በውጭ ሀገር የምንገኝ ወገኖች በዚህ ችግር ምክንያት የተፈጠሩ እንቅፋቶች ሳይገድቡን አጋጣሚውን ወደ ውጤታማ እርምጃ እንዲያሸጋግረን  የቅንጅትን መርሆ በማላበስ በአስቸኳይ ልዩነታችንን ማቻቻልና ሀይላችንን ማስተባበር ይጠበቅብናል። የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ አካሎች፤ ግለሰቦችና የዲሞክራሲ መርሆችን የሚያራምዱ ሁሉ በዚህ አጋጣሚ ለሌሎች መሰል ሀይሎች እጃቸውን በመዘርጋትና በመቀራረብ አዲስና የጠነከረ የዲሞክራቲክ እንቅስቃሴ መፍጠር አለባቸው። ከዚህ ሂደት ውጭ የገዡውን መንግሥት ከመጥቀም በስተቀር ትግሉን ወደፊት ለማራመድ አይረዳም። አልያም ከተከሰሱት ችግሮች ትምህርት በመቅሰም የተሻሉ የአሠራር ዘዴዎችና የአፈፃጸም ሥልቶች መቀየስ ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በየታሪክ አጋጣሚው በደሙ እየከፈለ ሊያገኝ የሞከረውን ሁለ ገብ ነፃነት በአምባገነኖችና በሆድ አደሮች ቢነጠቅም፤ ለፖለቲካ ፤ ለሶሻልና ለኢኮኖሚ ፍትህ ከሚያደርገው መራራ ትግል ወደኋላ ብሎ አያውቅም።

በእኛ በኩል ፤ በተለይም በውጭው ዓለም የምንገኝ ወገኖች በሙሉ ከጠባብ ወገንተኝነት፤ ተራ ስድቦችና አሉባልታዎች ተላቀን መልካም ባህላችንና ታሪካችን ያወረሰንን በመጠቀም በሀገራችን የዲሞክራቲክ ለውጥ እንዲመጣ በተቻልን አቅም ማገዙ ከሚጠበቅብን ግዴታዎች በጣም አነስተኛው ነው እንላላን።